በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3-0/253/07
Ref. No
ቀን 09 ሐምሌ 2007
Date

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት፤

ጉዳዩ፡- መመሪያ ስለመላክ፤

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አማካኝነት የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን መመሪያ ቁጥር 41/2007 ወጥቷል፡፡

በዚህም መሰረት ይህንኑ መመሪያ ለአፈፃፀም በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት የላክን ሲሆን በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የመረጃ ልውውጥና አያያዝ ስርአታችን፣ አደረጃጀታችን የተጠናከረና የተሟላ እስኪሆን በመመሪያው መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡት ተሽከርካሪዎች በማእከል በአ.አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብቻ የሚፈቀድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ካይዳኪ ገዛኸኝ
ም/ዋና ዳይሬክተር
የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና
... ራዎች ዘርፍ

ግልባጭ፤
- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር
- ለሕግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳዮች ቅ/ጽ/ቤት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፤

ይ/አ

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!

ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

1/ቀ/2033
30/10/07


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development


ቁጥር / Ref. No. 7/ኤፊ/2/75
ቀን / Date 24/10/2007

**ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

የአካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ የሚወስን የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2007 መውጣቱ ይታወቃል፡፡

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ከንዑስ አንቀጽ 2 ቀጥሎ ንዑስ አንቀጽ 1 በሚል የተፃፈው የአፃፃፍ ግድፈት ስለሆነ ንዑስ አንቀጽ 3 ተብሎ እንዲነበብ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዋስይሁን አባተ
የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

ግልባጭ፣
- ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
- ለመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን
- ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
- <u>አዲስ አበባ</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

Lett.W/GT

17/10/07

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
**The Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**Ministry of Finance and Economic Development**

ገቢ 1968 19/10/07

ቁጥር Ref. No. ታ/ዓ7/ዐ6/5/639
ቀን Date 16/10/2007

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ወጥቷል።

ስለዚህ መመሪያውን ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
ለመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን
ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

Lett.W/GT

ስልክ TEL 251-11-155 24 00, 22 66 98 251-11-155 00 81, 83, 86, 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O. Box 1905, 1037
ፋክስ Fax. 251-11-155 13 55, 55 14 96 251-11-155 38 44
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

# አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2007

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. ፪
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

ሰኔ 2007
አዲስ አበባ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 1

# አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን <u>የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2007</u>

የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው አካል ጉዳተኞች በተሽከርካሪ በመታገዝ ከቦታ ወደቦታ በመዘዋወር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ በማድረግ ራሳቸውንና አገራቸውን እንዲጠቅሙ መንግሥት ተገቢውን እገዛ ማድረግ እንዳለበት በመታመኑ፣

አካል ጉዳተኞች ወደአገር የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የተሰጠው መብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 129 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. “አካል ጉዳተኛ” ማለት በተፈጥሮው፣ በሕመም ወይም በማናቸውም አደጋ ምክንያት ለዘለቄታው የአካል ጉዳት የደረሰበት፣ በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ድጋፍ የሚያስፈልገው፣ እና የደረሰበትን የአካል ጉዳት በዝርዝር የሚያሳይ በሐኪሞች ቦርድ የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ሰው ነው፡፡

2. “የተጣራ ገቢ.” ማለት የመብቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ተቀጣሪ ሠራተኛ ከሆነ ተገቢው የገቢ ግብር እና የጡረታ መዋጮ ከተቀነሰ በኋላ የሚከፈለው የተጣራ ወርሃዊ ገቢ ሲሆን፣በግል ገቢ በሚያስገኝ ወይም የንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ ባገኘው ገቢ ላይ ተገቢው ግብር ከተከፈለ በኋላ የሚያገኘው የተጣራ ገቢ ነው፡፡ የመብት ተጠቃሚው በጡረታ የሚተዳደር ከሆነ በየወሩ የሚያገኘው የጡረታ ክፍያ የተጣራ ገቢ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

3. “ተሽከርካሪ” ማለት ለግል አገልግሎት ብቻ የሚውል የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ ባለሁለት እግር ወንበር ወይም ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ልዩ አውቶሞቢል፣ እንዲሁም በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ምክንያት የማሽከርከር ችሎታ ለሌላቸው አካል ጉዳተኞች የሚያገለግል መደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን፣ የእነዚህ ተሽከርካሪዎች የሞተር ጉልበት በማናቸውም ሁኔታ ከ1600 ሲሲ (አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሲሲ) መብለጥ የለበትም፡፡

4. “የመብቱ ተጠቃሚ” ማለት የአካል ጉዳተኛ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት የሚጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት የሚችል ግለሰብ ነው፡፡

5. “የግል አገልግሎት” ማለት የመብት ተጠቃሚው ተሽከርካሪውን በራሱ ወይም በሌላ ሰው አሽከርካሪነት ለግል ጉዳዮች ከቦታ ቦታ በማንቀሳቀስ መጠቀም ሲሆን በማናቸውም ሁኔታ ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ፣ ለንግድ ሥራ ዓላማ ወይም ገቢ ለሚያገኝበት ማንኛውም ተግባር ማዋልን እንዲሁም ከራሱና ከቤተሰቡ ውጪ ሌሎች እንዲጠቀሙበት መፍቀድን አይጨምርም፡፡

6. “የሐኪሞች ቦርድ” ማለት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እውቅና በተሰጠው ሆስፒታል የተቋቋመ እና የአካል ጉዳተኝነት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት ወይም ማስረጃ መስጠት የሚችል አካል ነው፡፡

7. “የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት” ማለት በደረሰበት የአካል ጉዳት ምክንያት በሰው ሰራሽ የአካል እንቅስቃሴ ድጋፍ ወይም ሌላ መሣሪያ ወይም በሌላ ሰው ድጋፍ ካልሆነ በስተቀር ከቦታ ወደቦታ ለመንቀሳቀስ የማይችል አካል ጉዳተኛ ነው፡፡

8. “ቤተሰብ” ማለት የባለመብቱን የትዳር ጓደኛ፣ልጆችና የባለመብቱንና የትዳር ጓደኛውን ወላጆች ያጠቃልላል፡፡

9. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የባለሥልጣኑን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይጨምራል፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

10. "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

11. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በጉምሩክ አዋጅ፣ በጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብ ወይም ሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች የተሰጡ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ቅደመ ሁኔታዎች ለሚያሟላ የመብት ተጠቃሚ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወን እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ለማስገባት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

## 5. ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለማስገባት

የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ አሟልቶ ሲቀርብ፦

1. የመንቀሳቀስ ችግር ያለበት ሆኖ ለማሽከርከር አካላዊ ችሎታ ያለው አካል ጉዳተኛ ከሆነ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ አንድ ባለሁለት እግር ወንበር ወይም ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ልዩ አውቶሞቢል፣



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቢ.ተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 3
Ethiopian Revenue and Customs Authority Records & Documentation No. 3
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

2. በአካላዊ ችግር ምክንያት የማሽከርከር ችሎታ የሌለው እና የማሽከርከር ችሎታ እንደሌለው በሐኪሞች ቦርድ ምርመራ እንዲሁም በሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠለት አካል ጉዳተኛ ከሆነ ለግል አገልግሎት የሚውል አንድ መደበኛ አውቶሞቢል፣

ከቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት ይችላል።

## 6. <u>ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስገባት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

1. ማንኛውም የመብቱ ተጠቃሚ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ ማሟላት አለበት።

   ሀ. በዜግነት ኢትዮጵያዊ መሆን እና በሀገር ውስጥ ከሚኖርበት አካባቢ የሚመለከተው አስተዳደር የተሰጠ የነዋሪነት መታወቂያ ማቅረብ፣

   ለ. በአገር ውስጥ ከሚገኝ እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እውቅና ከተሰጠው ሆስፒታል አካል ጉዳተኛ መሆኑን እና የጉዳቱን ዓይነት የሚያረጋግጥ በሐኪሞች ቦርድ የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ፣

   ሐ. ከሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኝነት ማረጋገጫ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ፣

   መ. በስሙ የሚያስመጣውን ተሽከርካሪ እራሱ አካል ጉዳተኛው የሚያሽከረክረው ከሆነ ማሽከርከር እንደሚችል ከሚመለከተው የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ወይም መ/ቤት የተሰጠ ማረጋገጫ እና የታደሰ የመንጃ ፍቃድ ማቅረብ፣

   ሠ. ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም የሀይማኖት ተቋም የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣ወይም ያላገባ ከሆነ ይህንኑ የሚያስረዳ ደብዳቤ ከሚኖርበት አካባቢ የሚመለከተው አስተዳደር ማቅረብ፣

   ረ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካርድ (TIN) ማቅረብ፣

   ሰ. ተሽከርካሪውን ለመግዛት የሚችል መሆኑን ከሚከተሉት አማራጮች በአንዱ ማረጋገጥ አለበት።

1) የመብት ተጠቃሚው ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም በጡረታ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት የተከፈለው ደመወዝ ወይም የጡረታ አበል ለባለሁለት እና ለባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ለልዩ አውቶሞቢል ሲሆን የተጣራ ገቢው ቢያንስ 40,000 ብር (ብር አርባ ሺ.ህ) እና ለመደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን ደግሞ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 80,000 ብር (ብር ሰማንያ ሺ.ህ) መሆን ያለበት ሲሆን ከቀጣሪው አካል የደመወዙን ልክና በዚህ ደመወዝ ላይ ግብር የተከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም ከጡረታ አስተዳዳሪው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ እና የጡረታ አበል መክፈያ ደብተር ማቅረብ አለበት፡፡

2) የመብት ተጠቃሚው በግል ገቢ በሚያስገኝ ወይም የንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ውስጥ ለባለሁለት እና ለባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ለልዩ አውቶሞቢል ሲሆን ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 40,000 ብር (ብር አርባ ሺ.ህ) እና ለመደበኛ አውቶሞቢል ሲሆን ደግሞ ከግብር በኋላ የተጣራ ገቢው ቢያንስ 80,000 ብር (ብር ሰማንያ ሺ.ህ) መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

ሸ. የመብቱ ተጠቃሚ ጥያቄውን ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ወደኋላ በሚቆጠር 10(አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ በስሙ ምንም ዓይነት የግል መገልገያ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያላስገባ መሆኑን፣ከቀረጥ ነፃ የሚያስገባውን ተሽከርካሪ እራሱ የሚያሽከረክር ወይም በአካል ጉዳቱ ምክንያት ራሱ ማሽከርከር የማይችል ከሆነ ተሽከርካሪው ከራሱ ጥቅም ወጪ ለሌላ ሰው ጥቅም እንደማይውል እና በሌላ ሰው የሚሽከረከር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የሚጠየቀውን በሙሉ ለመፈጸም እንዲሁም ለግል አገልግሎት ብቻ የሚጠቀምበት ለመሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ ማረጋገጥ አለበት፡፡

ቀ. በተሽከርካሪው አካል ላይ በሚመለከተው የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የሚያደረገውን ልዩ ምልክት በፍቃደኝነት የሚቀበል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

በ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ለ፣ ሐ ፣መ እና ሠ ላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ከዋናው ሰነድ በተጨማሪ ሰነዶቹን ከሰጡት መ/ቤቶች ወይም አካላት የሰነዶቹ ቅጂ በፋክስ መልዕክት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ መድረስ አለባቸው፡፡

ተ. የመብቱ ተጠቃሚ ተሽከርካሪውን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት የሚችለው በአካል ቀርቦ የሚጠበቅበትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ሲችል ብቻ ሲሆን ማናቸውንም ተግባር በውክልና ማከናወን አይቻልም።

ቸ. ባለትዳር የሆኑ የመብት ተጠቃሚዎች ሁለቱም የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው በመሆናቸው ምክንያት በተናጠል ባለሁለት እግር ወንበር ወይም ባለሦስት እግር ወንበር ባለሞተር ተሽከርካሪ ወደአገር ከሚያስገቡ በስተቀር እንደሁኔታው በቤተሰብ ከአንድ ልዩ ወይም መደበኛ ተሽከርካሪ በላይ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ማስገባት አይቻልም።

2. የሌላ አገር ዜጋ የሆነ ትውልደ ኢትዮጵያዊ አካል ጉዳተኛ በቋሚነት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ወደ አገር ጠቅልሎ መግባቱን፣ ይኖርበት ከነበረው አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ የተሰጠ ማስረጃ ሲያቀርብ እና ኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ከሚኖርበት የአካባቢ አስተዳዳሪ በቋሚነት ቢያንስ አንድ ዓመት የኖረ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ሲያቀርብ እና በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች ሲያሟላ አንድ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ሊፈቀድ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣

ሀ. ተጠቃሚው በአካላዊ ችግር ምክንያት ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ተሽከርካሪ የማሽከርከር ችሎታ የሌለው በመሆኑ በሾፌር የሚያንቀሳቅስ ከሆነ ከአሽከርካሪው ጋር ሕጋዊ ውል በመግባት እና ውሉ በተፈጸመ በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የውሉን ዋና ቅጂ እና የአሽከርካሪውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካርድ (TIN) ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት። ሕጋዊ ውሉ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካርድ (TIN) በማናቸውም ጊዜ በተሽከርካሪው ውስጥ ሊቀመጥ እና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማሳየት አለበት።

ለ. በአካላዊ ችግር ምክንያት ተጠቃሚው ከቀረጥ ነጻ ያስገባውን ተሽከርካሪ የማሽከርከር ችሎታ የሌለው በመሆኑ በቤተሰብ አባል የሚያንቀሳቅስ ከሆነ አስቀድሞ በሚመለከተው መስተዳድር የተረጋገጠ እና የቤተሰብ ዝርዝርን (ያለውን የቤተሰብ ግንኙነት ጨምሮ) የያዘ ሕጋዊ ሰነድ ለሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት።

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩት ማስረጃዎች በማናቸውም ሁኔታ ተሽከርካሪው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቆ ለነፃ ዝውውር ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ1(አንድ) ወር ጊዜ ውስጥ ለሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መቅረብ ያለባቸው ሲሆን፣ በማንኛውም ሁኔታ የሚደረጉ/የተደረጉ ለውጦች በሚመለከተው አካል ከሚቀርብ ማስረጃ ጋር ለውጡ በተደረገ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሠራተኛ እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መቅረብ አለባቸው፡፡

መ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከቱት ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ አንድን ከቀረጥ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ ሲንቀሳቀስ የተገኘ እንደሆነ፣ በጉምሩክ ሕጉ መሠረት ከቀረጥ ነጻ የገባ ዕቃ ያለአግባብ እንደመጠቀም ተቆጥሮ ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

## ክፍል ሦስት

## <u>መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 7. <u>የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

1. የመብቱን ተጠቃሚዎች በልዩ ሁኔታ ለማስተናገድ እንዲቻል የተለየ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማስፈፀሚያ ኮድ (Customs Procedure Code) ማዘጋጀት እና ዲክለራሲዮን ተሞልቶ ደጋፊ ሰነዶቹ ተያይዘው ሲቀርቡ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈፀም ማድረግ አለበት፡፡

2. የመብቱ ተጠቃሚ በቀረጥና ታክስ ነፃ ለመስተናገድ እና ተሽከርካሪውን ለመረከብ በአካል እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡

3. የመብቱ ተጠቃሚ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ጥያቄ ሲያቀርብ በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች መመሪያዎች ባለፉት 10(አሥር) ዓመታት ጊዜ ውስጥ በስሙ የግል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያላስገባ ስለመሆኑ በስም፣ በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና በጉምሩክ ኮድ (CPC) ያረጋግጣል፡፡

4. የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ ማሟላቱ ሲረጋገጥ ተሽከርካሪውን ለማስገባት የሚያስችለውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እንዲችል ለሚመለከተው ባንክ የቀረጥ ነፃ መብቱ የተፈቀደለት መሆኑን በደብዳቤ ይገልፃል፣ ይህንኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፡፡

5. በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመብቱ ተጠቃሚ አንድ ተሽከርካሪ ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲያስገባ ያደርጋል፡፡

6. ከቀረጥ ነፃ የገቡትን ተሽከርካሪዎች በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ በማደራጀት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለተገቢው ዓላማ እየዋሉ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡

7. የመብቱ ተጠቃሚ ይህን መመሪያ ወይም ሌሎች የጉምሩክ ሕጎችን ጥሶ ሲገኝ ተሽከርካሪውን በሕግ ቁጥጥር ሥር በማዋል አሰፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

8. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት ተሽከርካሪዎች ወደ ሌላ ወገን ለማስተላለፍ የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን በመቆጣጠር እና አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ ያስፈፅማል፣ ይህንኑ ለሚኒስትሩ ያሳውቃል፡፡

## 8. <u>የሠራተኞና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

1. በአካል ጉዳተኞች የሚቀርቡ የሕክምና ማስረጃዎችን በመመርመር፣ በሕግ ዕውቅና ከተሰጣቸው እና ከሚመለከታቸው የአካል ጉዳተኞች ተቋማት ጋር መረጃ በመለዋወጥ እና ተገቢውን ምርመራ እና ቁጥጥር በማድረግ የመብቱ ተጠቃሚ አካል ጉዳተኛ መሆኑን እና የጉዳቱን ዓይነት በመጥቀስ የድጋፍ ደብዳቤ ዋና ቅጂ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሚኒስትሩ ይልካል፣ ትክክለኛነቱን ለማመሳከር የዋናውን ሰነድ ቅጂ በፋክስ መልዕክት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስተላልፋል፡፡

2. የመብቱ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ መሠረት ላስገባው ተሽከርካሪ ዓመታዊ ዕድሳት የድጋፍ ደብዳቤ ለሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ ዋና ቅጂ ይልካል፣ ዋናውን ቅጂም በፋክስ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለዓመታዊ ዕድሳት ለሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮዎች የድጋፍ ደብዳቤዎች የተፃፈላቸውን እንዲሁም በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪ አስገብተው ለዓመታዊ ዕድሳት የድጋፍ ደብዳቤ ያላፃፉትን የመብት ተጠቃሚዎች በመለየት ዝርዝራቸውን ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የዕድሳት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኂላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስትሩ እና ለባለሥልጣኑ ይልካል፡፡

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚረከባቸውን ሕጋዊ ውሎች እና ሌሎች ሰነዶች ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ የዋናውን ሰነድ ቅጂዎች ለባለሥልጣኑ እና ለክልልና ከተማ ትራንስፖርት ቢሮዎች ይልካል።

5. በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ በማስገባት ተጠቃሚ የሚሆኑ አካል ጉዳተኞችን ዝርዝር መረጃ ያደራጃል።

## 9. <u>የክልልና የከተማ ትራንስፖርት ቢሮዎች</u>

1. የሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ የመብቱ ተጠቃሚ ጥያቄ ሲያቀርብ በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ተሽከርካሪዎች ማሽከርከር እንደሚችል የሚያሳይ የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ መንጃ ፍቃድ የሰጠበትን ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት እንዲሁም የመንጃ ፈቃዱ የታደሰ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ዋናውን ቅጂ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ይልካል፣ ትክክለኛነቱን ለማመሳከር የዋናውን ሰነድ ቅጂ በፋክስ መልዕክት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስተላልፋል።

2. ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን የተፈቀደውን ተሽከርካሪ ለመለየት የሚያስችል በተሽከርካሪው አካል ላይ በሚታይ ቦታ የአካል ጉዳተኞችን ምቹ ሁኔታ የሚገልጽ ዓለም አቀፍ ልዩ ስሌዳ ወይም ሊለወጥ የማይችል ልዩ ምልክት ያደርጋል።

3. የሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ መመሪያ መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ለዓመታዊ ዕድሳት ሲቀርቡ ከሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። የሚቀርቡትንም የድጋፍ ደብዳቤዎች ዋና ቅጂ በፋክስ መልዕክት እንዲረጋገጡ ያደርጋል።

4. የሚመለከተው የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለዓመታዊ ዕድሳት የቀረቡ የመብት ተጠቃሚዎችን እና የተሽከርካሪዎቻቸውን ዝርዝር የዓመታዊ ዕድሳት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስትሩ እና ለባለሥልጣኑ ይልካል።

## 10. <u>የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም የጤና ተቋማት</u>

1. ለአካል ጉዳተኞች የሐኪሞች ቦርድ መረጃ ለመስጠት የሚችሉ ዕውቅና ያላቸውን ሆስፒታሎች በመለየት ዝርዝራቸውን ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያስተላልፋል።

የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
1

2. የሜዲካል ቦርድ መረጃ ለአካል ጉዳተኞች መስጠት ያቆሙ ወይም እንዲያቋርጡ የተደረጉ ሆስፒታሎችን ዝርዝር በወቅቱ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ያሳውቃል፡፡

3. የጤና ምርመራ ያደረገው ሆስፒታል የሐኪሞች ቦርድ የሕክምና ማስረጃውን ዋና ቅጂ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ይልካል፣ትክክለኛነቱን ለማመሳከር የዋናውን ሰነድ ቅጂ በፋክስ መልዕክት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ያስተላልፋል፡፡

## 11. <u>የፖሊስ አካላት</u>

የፓሊሲ አካላት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጪ ውለው በመገኘታቸው እንዲያዙ ከባለሥልጣኑ የትብብር ጥያቄ ሲደርሳቸው ተሽከርካሪዎችን በመያዝ በአቅራቢያ ላለው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ እና የድርጊቱ ተሳታፊዎችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በማሳወቅ ይተባበራሉ፡፡

## 12. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር</u>

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው አካላት የሚላኩ ሪፖርቶችን እና መረጃዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፡፡

2. በሚቀርቡ ሪፖርቶች እና መረጃዎች መሠረት ከባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ጋር በመሆን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 13. <u>መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት  የወል ተግባር</u>

በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 7 እስከ 11 በተደነገገው መሠረት ይህንን መመሪያ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ጉዳይ እንዲያስፈጽሙ የተወከሉ ኃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች እና በአማራጭ/በምትክነት የሚሰሩ ሌሎች ተወካዮችን ጨምሮ ስም፣ የሥራ ኃላፊነት፣ የፊርማቸው ናሙና፣ የስልክ ቁጥር፣ ፋክስ

እና ኢ-ሜይል አድራሻቸውን የያዘ ሰነድ ለባለሥልጣኑ፣ ለሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም ይህ መመሪያ ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ያሳውቃሉ፤ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችም ሲቀየሩ በተመሳሳይ የተቀየሩትን እና የተኳቸውን ኃላፊ ሙሉ አድራሻ በዚህ የመመሪያው ክፍል ለተመለከቱት አካላት በሙሉ ያሳውቃሉ፡፡

# ክፍል አራት

## ከቀረጥና ታክስ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች ስለሚተላለፉበት ሁኔታ

### 14. ተሽከርካሪዎችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ

1. በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ የሆነ አካል ጉዳተኛ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባውን ተሽከርካሪ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚችለው ቢያንስ ተሽከርካሪው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አጠናቆ ለነፃ ዝውውር ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር 5 (አምስት) ዓመት በኋላ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው፡-

   ሀ) ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ላለውና የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚያሟላ አካለ ጉዳተኛ ብቻ ነው፡፡

   ለ) ሆኖም ተሽከርካሪው የሚተላለፈው ተመሳሳይ የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሌላ ሰው ከሆነ ባለው የጉምሩክ ሕግና መመሪያ መሠረት ከተሽከርካሪው ዋጋ ላይ የእርጅና ቅናሽ ተደርጎ የሚሰላውን ቀረጥና ታክስ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በመክፈል ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ቢኖሩም የመብቱ ተጠቃሚ የሆነው ሰው የ5 ዓመት የጊዜ ገደቡ ከመድረሱ ወይም ከመጠናቀቁ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ሥልጣን ካለው ፍ/ቤት በሚያቀርቡት የወራሽነት ማረጋገጫ መሠረት ወራሹ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ ከመኪናው ዋጋ ላይ የእርጅና ቅናሽ ከተደረገ በኋላ በሚሰላ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ አስፈላጊ የሆነውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሲከፈል ተሽከርካሪው ለሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሕጋዊ ወራሽ ወይም ወራሾች ቀረጥና ታክሱን መክፈል ካልቻሉ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በማስወረስ ተሽከርካሪው ተሸጦ ከሽያጭ ዋጋው ላይ ቀረጥና ታክሱ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ እንዲሰጠው/ጣቸው ማድረግ ይቻላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 ድንጋጌዎች ቢኖሩም ተሽከርካሪን ከመብት ተጠቃሚ ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚቻለው በተጠቃሚው ወይም በሕጋዊ ወራሹ ወይም ወራሾቹ የጽሑፍ ማመልከቻ እና አስፈላጊ ማስረጃዎች ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## <u>ልዩ ልዩ</u>

### 15. <u>ክልከላ</u>

ማንኛውም የመብት ተጠቃሚ በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች መመሪያዎች ጥያቄውን ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚቆጠር 10(አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ በስሙ የግል ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያስገባ ከሆነ በድጋሚ ተሽከርካሪ ማስገባት አይችልም፡፡

### 16. <u>ተጠያቂነት</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ያስገባ የመብት ተጠቃሚ ተሽከርካሪውን ከራሱ ውጪ ወይም በአካላዊ ችግር ምክንያት የማሽከርከር ችሎታ የሌለው ከሆነ ተሽከርካሪውን ለራሱ ጥቅም ከሚያውል በስተቀር በሌላ ሰው ሲሽከረከር እና በዚህ መመሪያ ከተደነገገው ውጪ ለሌላ ጥቅም ቢውል ወይም ለሌላ ወገን ተላልፎ ቢገኝ አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 17. <u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

የዚህ መመሪያ ተጠቃሚ ለመሆን መብት ያለው ሰው በመብቱ እንዳይጠቀም የተደረገ ከሆነ አቤቱታውን ወይም ይግባኙን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 154 እና 155 መሠረት እንደአግባብነቱ ለአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም ለግብር ይግባኝ ጉባዔ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

### 18. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና ሰርኩላሮች</u>

በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ጉዳዮች የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች ወይም የአሠራር ልምዶች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 3

19. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 16 ቀን 2007 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር